የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፵፮
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፪ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24th Year No.46
ADDIS ABABA 29th June, 2018

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፹፰/፪ሺ፲ ዓ.ም

ሕገ መንግስቱን እና ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን ከአደጋ ለመከላከል የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፪/፪ሺ፲ ለመቀበልና ለማፅደቅ የወጣውን አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፹፫/፪ሺ፲ ለመሻር የወጣ አዋጅ ……ገጽ ፲ሺ፫፻፺

## Content

Proclamation No.1088/2018

Proclamation to Repeal Acceptance and Approval of Proclamation No. 1083/2018 of State of Emergency Proclamation No. 2/2018 to defend the Constitution and Constitutional Order from Threat Proclamation ………………………….--Page 10390

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፹፰/፪ሺ፲

### ሕገ መንግስቱን እና ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን ከአደጋ ለመከላከል የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፪/፪ሺ፲ ለመቀበልና ለማፅደቅ የወጣውን አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፹፫/፪ሺ፲ ለመሻር የወጣ አዋጅ

በሀገራችን በሕገ መንግስቱና በሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱ ላይ ተጋርጦ የነበረው አደጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻል በማሳየቱ እና በመደበኛው የሕግ ማስከበር ሥርዓት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚቻልበት ደረጃ ላይ የተደረሰ በመሆኑ ሕገ-መንግስቱንና ሕገ-መንግስታዊ ሥርዓቱን ለመጠበቅና ከአደጋ ለመከላከል የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መሻር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

አሁን የታየውን አንፃራዊ ሠላም በመንግስትና በሀገራችን ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀጥተኛ ተሳትፎ እና ባለቤትነት በማረጋገጥ የተጀመረውን ልማትና ዲሞክራሲ ማስቀጠል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት ይህን አዋጅ አውጥቷል::

### Proclamation No.1088/2018

### A PROCLAMATION TO REPEAL ACCEPTANCE AND APPROVAL OF PROCLAMATION No. 1083/2018 OF STATE OF EMERGENCY PROCLAMATION No. 2/2018 TO DEFEND THE CONSTITUTION AND CONSTITUTIONAL ORDER FROM THREAT

WHEREAS, it has been found necessary to repeal State of Emergency Proclamation issued to Defend the Constitution and Constitutional Order from threat as the dangers posed against the Constitution and Constitutional Order are improved from time to time, and the condition is reached at the level where it can be prevented and controlled by the regular law enforcement system;

WHEREAS, it has been found necessary to ensure the existing relative peace by direct participation and ownership of the government and nation, nationalities and peoples of the country and sustain the commenced development and democracy;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ሕገ መንግስቱን እና ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን ከአደጋ ለመከላከል የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፪/፪ሺ፲ ለመቀበልና ለማፅደቅ የወጣውን አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፹፫/፪ሺ፲ ለመሻር የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፹፰/፪ሺ፲"ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### ፪. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለመሻር

### ፫. የተሻሩ ሕጎች

፩/ ሕገ መንግስቱንና ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን ከአደጋ ለመከላከል የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፪/፪ሺ፲ ለመቀበልና ለማጽደቅ የወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፹፫/፪ሺ፲ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ ሕገ መንግስቱን እና ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን ከአደጋ ለመከላከል የወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፪/፪ሺ፲ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፬. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

የፍትህ አካላት ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ አፈፃፀም ጋር ተያይዞ የጀመሯቸው በመደበኛ የፍትህ ሥርዓት ሊታዩ የሚችሉ ጉዳዮች በመደበኛው የፍትህ ሥርዓት እንዲጠናቀቁ ይደረጋል፡፡

### ፭. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

፩/ ሕገ መንግስቱንና ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን ከአደጋ ለመከላከል የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፪/፪ሺ፲ ማስፈፀሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፳፬/፪ሺ፲ በዚህ አዋጅ የተሻረ በመሆኑ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

፪/ በአስቸኳይ ጊዜ ኮማንድ ፖስት የወጣው የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር ፩/፪ሺ፲ በዚህ አዋጅ የተሻረ በመሆኑ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Proclamation to Repeal Acceptance and Approval of Proclamation No. 1083/2018 of State of Emergency Proclamation No. 2/2018 to defend the Constitution and Constitutional Order from Threat Proclamation No. 1088/2018".

### 2. Scope of Application

This Proclamation shall be applicable in all parts of the country.

## PART TWO
## REPEAL

### 3. Repealed Laws

1/ The Proclamation No. 1083/2018 issued to accept and approve the Constitution and Constitutional Order Defence from Threat State of Emergency Proclamation No.2/2018 is hereby repealed.

2/ The Constitution and Constitutional Order Defence from Threat State of Emergency Proclamation No.2/2018 is hereby repealed.

## PART THREE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 4. Transitory Provisions

Cases started by Justice Organs during implementation of the Emergency Proclamation, subject to regular justice system, shall be finalized in accordance with the regular justice system.

### 5. Inapplicable Laws

1/ The Constitution and Constitutional Order Defence from Threat State of Emergency Proclamation No.2/2018, and Council of Ministers Regulations No. 424/2018 to implement same is hereby repealed and inapplicable.

2/ The State of Emergency Measures Implementation Directive issued by State of Emergency Command Post No. 01/2010 is hereby repealed and inapplicable.

**፮. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከታወጀበት ግንቦት ፳፰ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፪ ቀን ፪ሺ፲ ዓ/ም**

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**6. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force from 5th day of June, 2018 as it is declared by the House of Peoples Representatives.

**Done at Addis Ababa, this 29th day of June, 2018.**

**MULATU TESHOME (Dr.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**